# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፦** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ሐምሌ 28 ቀን 2004 ዓ.ም**

**በሞያሌ ባልታወቀ ኃይል ከባድ ጥቃት ተሰነዘረ፤**

**ከ50 ሰዎች በላይ ተገደሉ በአንድ ጉድጉዋድ የ20 ሰው አስከሬን ተቀበረ፤**

**አንድ ወታደራዊ ካምፕ ሙሉ ለሙሉ ወደመ፤**

**በአዳማ ሹም ሽረት ተደረገ፤**

ወያኔ በፈጠረው ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው ምክንያት ከ20 ዓመታት በላይ የስቆጠረው የእርስ በርስ ግጭት ሰሞኑን በቦረና ድንገት ተከስቶ ከ50 ሰዎች በላይ ለሞት ሲዳገሩ በመቶዎች የሚቆጠሩት ደግሞ መቁሰላቸውን ከሰፍራው የደረሰን ጥቆማ ገለፀ፡፡

ረቡዕ ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀትር በሁዋላ በተፈጠረው በዚሁ ግጭት ከሞቱት እና ከቆሰሉት በተጨማሪ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች ወደ ጎረቤት ሀገር የሸሹ ከመሆኑም በላይ በግጭቱ ቤት ንብረቶቻቸው እና ከብቶቻቸው እንደተቃጠሉባቸውም ከስፈራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል፡፡

በዕለቱ በ5 ሰዓት ገደማ በ10 የጭነት መኪና ተጭኖ የመጣ አንድ ታጣቂ ቡድን ከጎረቤት ሀገር ሱማሊያ በዶሎ በኩል ወደ ቦረና መግባቱን የጠቀመው የደረሰን ዘገባ በስፍራው ለሰዓታት ጥናት ሲያደርግ ከቆየ በሁዋላ ቀትር ላይ በከፈተው ድንገተኛ ተኩስ ከ50 ሰዎች በላይ የተገደሉ መሆኑን ጠቅሶ በቦታው የነበሩ ጥቂት የፌዴራል ፖሊሶችም የዚሁ ተኩስ ሰለባ እንደሆኑም ገልጾዋል፡፡

በወቅቱ የመቁሰል አደጋ ከደረሰባቸው ሰዎች መሀከል ብዙዎቹ ወደ ያቤሎ ከተማ ህክምና እንዲያገኙ የተወሰዱ ቢሆንም ከቁስለኛው ብዛት የተነሳ ሁሉንም ማዳረስ ባለመቻሉ ብዙዎቹ ህክምና ሳያገኙ መሞታቸውንም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

በተከፈተው ተኩስ በሰው ላይ ጉዳት ከመድረሱም በላይ የወረዳው ፖሊስ ጽህፈት ቤት......ንግድ ባንክ እና የንግድ ሱቆች ላይ ጥቃት ተሰንዝሮ ንብረቶች ከመውደማቸውም በተጨማሪ ጥበቃ ላይ የነበሩትን አስረው የወሰዱዋቸው ሲሆን የዲላ ንግድ ባንክ ሰራተኛ የሆነ አንድ ባለስልጣን ድንገት ተኩስ በተከፈተበት ወቅት ሞያሌ ከተማ በመገኘቱ መኪናውን ሲያሽከረክር ከነበረው ሹፌር ጭምር ተፍኖ ወዳልታወቀ ስፍራ መወሰዱንም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ጥቃት ሰንዛሪው ቡድን እራሱን በማይገለጽ ሁኔታ ተሸፋፍኖ እና እራሱን ደብቆ የመጣ መሆኑን የጠቆሙት የአካባቢው  ነዋሪዎች እርስ በርስ በሚነጋገሩበት ወቅት ቋዋንቋዋቸው ፍጹም የማይገባና የማይታወቅ መሆኑን ጠቅሰው አላህ አክበር! እያሉ የእሩምታ ተኩስ ሲከፍቱ እንደነበረም የአካባቢው ተወላጆች ሲናገሩ ተደምጠዋል::

በጨሙ.....ሸዋበሬና መላቡ ቀበሌዎች የተጀመረው ይሄው ድንገተኛ ተኩስ ቀስ በቀስ ወደ ሞያሌ ከተማ ተሸጋግሮ ሙሉ ለሙሉ ለ24 ሰዓታት ታጣቂው ቡድን ተቆጣጥሮ የነበረ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ለረዥም ሰዓታት በሞያሌ በቆየባቸው ወቅት በከተማዋ ኮረብታ ላይ የሚገኘው ወታደራዊ ካምፕ ሙሉ ለሙሉ የወደመ ሲሆን በመንግስት ንብረቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱንም ነዋሪዎቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በዚሁ ድንገተኛ ጥቃት የተገደሉ ዜጎች በአንድ ጉድጉዋድ ከ20 ሰው በላይ የተቀበረ መሆኑን የጠቆሙት ነዋሪዎቹ  ጥቃቱ ያነጣጠረው በፌዴራል ፖሊስ በመከላከያና በወያኔ ካድሬዎች ላይ ብቻ እንደነበር የሞያሌ ከተማ ነዋሪዎች ገልጸዋል::

ከኬንያ ጋር በድንበር ከተማነት እና በደረቅ ወደብነት በማገልገል ላይ ያለችው ሞያሌ ከተማ የኦሮሚያ እና የሱማሌ ክልል መንግስታት በጋራ የሚያስተዳድሩዋት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ህዝቡም በሁለት ተከፍሎ የሚተዳደር መሆኑም ይታወቃል::

እብሪተኛው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የአሜሪካንን ፍላጎት ለማሙዋላት ሲል ብቻ ያለ ኢትዮጵያ ህዝብ ይሁንታና ፍቃድ በጎረቤት ሀገራት እየገባ ሲፈተፍት መቆየቱን ያስታወሱት የሞያሌ ከተማ ነዋሪዎች ወያኔ በፈጠረው ችግር ምክንያት እራሱን አልሻባብ ብሎ የሚጠራው ቡድን ግዜ ጠብቆ ጥቃት የሰነዘረ መሆኑን ገልፀው አሁን በታየው ሁኔታ ወደፊትም አስጊ መሆኑን ገልጸዋል::

ይሄ ታጣቂ ቡድንም እራሱን አልሻባብ ብሎ የሚጠራው ቡድን አንዱ አንጃ ሳይሆን እንዳልቀረ የጠቆሙት የሞያሌ ከተማ ነዋሪዎች ጥቂት የፌዴራል ፖሊስ አባሎችን...... የንግድ ባንክ ሰራተኞችን እና የኦሮሚያ ፖሊስ አባሎችን አፍኖ ሲወስድ ከከተማዋ ነዋሪዎች ግን አንድም ሰው አለመውሰዱ ቡድኑ ለዘረፋ ሳይሆን ለፖለቲካ ፍጆታ የመጣ መሆኑን ያመላከተ ነው ሲሉ ይናገራሉ::

እንደ ሞያሌ ከተማ ነዋሪዎች ገለጻ ከሆነ ወያኔ ወደ ስልጣን ላይ ከወጣበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የገሪና የቦረና ጎሳዎች በየግዜው የሳር መሬት ይገባኛል ጥያቄ እያነሱ እርስ በርስ እንደሚጋጩ አስታውሰው ይሄ ግን የገሪና የቦረና ጎሳ ግጭት ሳይሆን እራሱን ባደራጀ ታጣቂ ቡድን የተሰነዘረ ጥቃት መሆኑን አስረግጠው ይናገራሉ::

ይሄንኑ ሲያጠናክሩ  ቡድኑ የሚናገረው ቁዋንቁዋ የአረብኛ የሚመስል ከመሆኑም በተጨማሪ ተኩስ ሲከፍት አላህ አክበር እያለ እንደነበር ጠቅሰው የታጠቀው መሳሪያም ላውንቸር.....አርፒጂ.. የእጅ ቦምብና ሌሎችም ከቀላል እስከ ቡድን መሳሪያ ታጥቆ እንደነበር የአይን እማኞቹ ገልጸዋል::

ቡድኑ ጥቃቱን አድርሶ ከሄደ ከስድስት ሰዓት ቆይታ በሁዋላ የፌዴራል ፖሊስ እና የመከላከያ ሰራዊት በአምስት አራል ራሽያ ሰራሽ መኪና ተጭኖ የመጣ መሆኑን የጠቆሙት የሞያሌ ከተማ ነዋሪዎች ይሄው ቡድን ገና ከተማ እንደገባ ነዋሪዎችን ከማረጋጋት ይልቅ እያሸበረ.....የኦነግ ተቀጽላ ነህ.....የአልሻባብ ተላላኪ ነህ .....በሚል ነዋሪውን ወጣት .....አሮጊት.....ሽማግሌ....አዛውንት ሳይል በዱላ መቀጥቀጡን ነዋሪዎች እያነቡ ሲናገሩ ተደምጠዋል::

በዚህም ብስጭት ብዙዎቹ የሞያሌ ከተማ ነዋሪዎች የእለት ልብሳቸውን ብቻ እየያዙ ወደ ጎረቤት ሀገር ኬንያ የተሰደዱ ከመሆኑም በላይ ከሞያሌ ዙሪያ ከሚገኙ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ከ35 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን  ወደ ጎረቤት ሀገር ኬንያ መግባታቸውንና በአንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ መጠለላቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አረጋግጦዋል::

የወያኔ ቡድን ለዜጎች ካለው ንቀት እና ጥላቻ  የተነሳ ገና ከተማዋን በተቆጣጠረበት ሰከንድ ህዝቡን የቁም ስቅሉን እያሳየ እንደነበርና ይባስ ብሎ የታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ግንኙነት አላችሁ እያለ ማንገላታቱ አስገራሚ ብቻ ሳይሆን አስደንጋጭ ነው ያሉት የሞያሌ ነዋሪዎች በአሁኑ ሰዓትም ታጣቂ ቡድኑ ከፈጸመው ሽብር በላይ መከላከያና ፌዴራል ፖሊስ በህዝቡ ላይ እየፈጸመ የሚገኘው እንደሚበልጥም ጨምረው ገልፀዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ህዝብ ሳያውቅ እና ሳይፈቅድ በማን አለብኝነት በጎረቤት ሀገር ሱማሊያ ጦሩን አስገብቶ ሲፈተፍት ዘላቂ ጠላት ለሀገሪትዋና ለህዝቦችዋ ሊገዛ ይችላል ከዚህ ተግባሩ ሊታቀብ ይገባል ሲሉ ምሁራኖች እና ህዝቦች ሲወተውቱ እንዳልነበር በሞያሌም የታየው እውነታ ይሄው መሆኑን ገልጸው ወያኔ የዕለት እንጂ አርቆ መመልከቻ አዕምሮ የሌለው መሆኑን ያሳየ ነው ብለዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ  የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በደረሰበት ድንገተኛ ህመም ለህክምና ወደ ውጭ ሀገር ከወጣበት  እና ስልጣኑን ለህወሀቱ ለዶ/ር ቲዎድሮስ አድህኖም ካስረከበበት ግዜ ጀምሮ በወያኔ ቡድን ውስጥ ሽብርና ስጋት ተፈጥሮ አንዱ አንዱን የጎሪጥ መመልከት የተጀመረበት ወቅት ላይ ባለበት በአሁኑ ሰዓት በደኢህዴንና በኦህዴድ ውስጥ ባሉ ባለስልጣናት ላይ አዲስ ሹም ሽረት መደረጉን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገለጸ::

ደኢህዴን በአዋሳ...... ኦህዴድ በአዳማ ከተማ ዓመታዊ ጉባዔ በማካሄድ ላይ ባሉበት በዚህ ግዜ ስብሰባው ሊጠናቀቅ ጥቂት ቀን ሲቀረው አዲስ ሹም ሽረት መደረጉን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል::

በአዳማ በተደረገው የኦህዴዱ ዓመታዊ ጉባዔ ላይ 17 የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ከስራ እንዲባረሩ ከመወሰኑም በላይ እንደጥፋታቸው ለፍርድ እንዲቀርቡ ተብሎ በጉባዔው ውሳኔ ማግኘቱም ታውቆዋል፡፡

ከተባረሩት ባለስልጣናት መሀከል የኦሮሚያ ክልል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ታደለ ነጊሾ እና ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሰዒድ ጁንዲ የሚገኙበት ሲሆን ሌሎችም የቢሮ ኃላፊዎች ከስልጣናቸው እንደተነሱ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

የተባረሩት 17 ከፍተኛ ባለስልጣናት ከስራ መባረራቸው ብቻ ሳይሆን በህግ እንዲቀርቡ ተብሎ የፈጠራ ክስ ተመስርቶባቸው ለፍርድ ሊቀርቡ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በተለይ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንቱ ከተሾመ ጥቂት ግዜ ቢሆነውም ለህዝቡ እጅግ በሚገርም ሁኔታ ሲሰራ እንደነበርና ይህም ሁኔታ በወያኔ ባለስልጣናት ዘንድ ያልተወደደለት ከመሆኑም ባሻገር በአሁኑ ሰዓት ክልሉን በበላይነት እና በሞግዚት አስተዳደር ከሚመራው ገብረተንሳይ ወ/ተንሳይ ከተባለው የህወሀት ሰው ጋር ሊግባባ ባለመቻሉ ከስልጣኑ ሊነሳ ምክንያት እንደሆነም ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

በደቡብ ክልልም በተመሳሳይ ከአምስት ባለስልጣናት በላይ ከስራ ኃላፊነታቸው እንዲነሱ የተወሰነ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ወደፊት በግለሰቦቹ ላይ ክስ ተመስርቶ ህግ ፊት እንዲቀርቡ በሚል ውሳኔ መተላለፉንም ከአዋሳ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

ባለስልጣን ከወራት በላይ ሊያስቀምጥ ያልቻለው የአዳማ ከተማ ምክር ቤትም ሰሞኑን በተደረገ ሹም ሽረት አዲሱ ከንቲባ ከስልጣኑ ተነስቶ በምትኩ ከአርሲ አሰላ የአንድ መምሪያ ኃላፊ ተመርጦ መምጣቱንና መሾሙን ከአዳማ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

ከተሾመ ሁለት ወር ያልሞላው ለገሰ የተባለው ይሄው አፍለኛ ካድሬ የአዳማ ከንቲባ በአግባቡ ፋይሎችን አስተካክሎ ሳይጨርስ ሰሞኑን ከከንቲባነቱ የተባረረ ሲሆን በምትኩም ከአርሲ አሰላ ተመርጦ የተሾመበት መሆኑ ታውቆዋል፡፡

በመጨረሻም ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት መሪዎቻችንን እንመርጣለን ብለው ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበሩትን ሙስሊሞች በዱላና በጥይት ደብደበው አቁስለው መልሰው በግዳጅ ምስክር ትሆናላችሁ በማለት ሰሞኑን ሲያዋክቡዋቸው እንደነበር ተጋለጠ፡፡

መሪዎቻችን ይፈቱ ብለው በሰላማዊ መንገድ በታላቁ አንዋር መስጊድ ውስጥ ተቃውሞ ሲያሰሙ በነበሩት ሙስሊሞች ላይ ፖሊስ ግቢ ድረስ ገብቶ ድብደባ የፈፀመባቸው ዜጎች የሙስሊሙ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች የላኩት ቡድን ነው የደበደበን ብላችሁ መስክሩ ተብሎ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸውም ከቤተሰቦቻቸው የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ፡፡

በብሔራዊ መረጃና ደህንንነት ቢሮ አስተባባሪነት የተጀመረው ይሄው አዲስ የምስክር ማደራጀት ስራ በፖሊስ ተደብድበው በሆስፒታል ተኝተው የነበሩትን በመሉ እያስፈራሩ በሀሰት እንዲመሰክሩ

የተነገራቸው ሲሆን ለምትመላለሱበት ለእያንዳንዱ ቀን ለውሎ አበላችሁ 250 ብር ለእያንዳንዳችሁ እንከፍላለን እንደተባሉም ለቤተሰቦቻቸው ቅርበት ያላቸው ወገኖች ጥቆማ አጋልጠዋል፡፡

የሚመሩኝ ከፖለቲካ የጸዱ...... እምነቱን ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆን አለባቸው ብሎ ሙስሊሙ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ በማቅረቡ ብቻ የጥፋት ኃይሎች ያነሱት እና ያነገቡት አጀንዳ ነው በሚል የህዝበ ሙስሊሙን ጥያቄ ለማዳፈን ላይ ታች እየዳከሩ ቢሆንም ውጤቱ ግን የከፋ ደረጃ ሊደርስ እንደሚችል ከወዲሁ እየተነገረ ይገኛል፡፡

ከትናንት በስቲያ ዓርብ ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም እንደ ሌላው ግዜ ሁሉ ሙስሊሙ በአንዋር መስጊድ ውስጥ በወያኔ ላይ ተቃውሞ መስተጋባቱም ታውቆዋል፡፡

ሙስሊሞቹ የሰላት ስነ ስርዓታቸውን እንዳጠናቀቁ ሁሉም በያሉበት በመቀመጥ ሁለት እጆቻችን ወደ ላይ በማውጣት ለአምላካቸው በምልክት ልመና ያካሄዱ ከመሆኑም በላይ አፋቸውን በሁለት እጆቻቸው በመያዝ እንዳንናገር ታፍነናል የሚል መልዕክት ማስተላለፋቸውንም በቦታው ከነበረው ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

እንደ ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን እይታ ከሆነ ሙስሊሙ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ሁለት እጆቹን አመሰቃቅሎ ደረቱ ላይ በመለጠፍ እስረኛ ሆነናል የሚል መልዕክት ካስተላለፉ በሁዋላ ድንገት ሳይታሰብ ሁሉም በአንድ ግዜ ቅልጥ ያለ ጩብጨባ በማሰማታቸው አካባቢው ሲናወጥ እንደነበርና ፌዴራል ፖሊሶቹን ጭምር ያስበረገገ እንደነበረ ጨምሮ ገልጾዋል፡፡

የሙስሊም መፍትሄ አፈላላፊጊ ኮሚቴ አመራሮች ከታሰሩ በሁዋላ ተቃውሞው ይቆማል ብሎ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበየሁ ሲደነፋ የነበረ ቢሆንም ሙስሊሙ ህዝብ ግን የታሰሩት ወኪሎቻችን ይፈቱ በማለት የተቃውሞ ስልቱን በመቀያየር ብሶቱን በአደባባይ ሲያሰማ እንደዋለም ዘጋቢያችን በስፍራው ተገኝቶ የተከታተለውን ዘግቦዋል፡፡